ኢዴኅ ኅብረሕዝብ

| የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት ＋ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፌዴራል ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ |
|---|

# <u>የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት (ኢዴኅ) እና የኢትዮጵያ ሕዝብ ፌዴራል ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ (ኅብረሕዝብ-ኢትዮጵያ) የውኅደት መግለጫ፡፡</u>

ቀደም ሲል በነበሩና አሁን ሥልጣን ላይ ያለው የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ባባሳቸውና በፈጠራቸው አዳዲስ ተጨማሪ ችግሮች ምክንያት አገራችን ኢትዮጵያ እጅግ ከባድ የፖለቲካ፥ የኤኮኖሚና የማኅበራዊ ቀውሶች ውስጥ ተዘፍቃለች፡፡ ይኸ መንግሥት ሆን ብሎ በሚከተላቸው ፖሊሲዎች ምክንያት በብሔረሰቦች መካከል አለመተማመን እንዲሰፍን ተደርጓል፡፡ በሚያሳፍር መልኩ አገራችንን ለአንድነት መናጋት፥ ሕዝቧን ለነጣ ድኅነትና የረሃብ አዙሪት፥ ለልዩ ልዩ ቀሳፊ ተውሳኮች፥ ለከፋ እርዛትና ለሥራ አጥነት፥ ለሰላም መጥፋትና ብሔራዊ ክብር መዋረድ ወዘተርፈ ዳርጓታል፡፡

ነባርና ሥር የሰደዱ ችግሮቻችንም ሆኑ እነኝህን ችግሮች እያባባሰና አዳዲስ ችግሮችንም እየፈለፈለ ባለው የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ተቀስፋ የተያዘችው ውድ አገራችንና ዜጎቿ በሙሉ እንጂ የተወሰነው የአገር ክፍል ብቻ አይደለም፡፡ ማንኛውም አካባቢ ከነኝህ ችግሮች የሚከልለው የብቻው አጥር ሰርቶ አይመለከተኝም ማለት ፈጽሞ አይችልም፡፡ ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ጎጠኛ መሆኑ ባይካድም በስሙ የሚነግድበትን የትግራይ አካባቢም እንኳ ያልጠቀመና ሊጠቅምም የማይችል መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ ይኸ ማንንም የማይጠቅም አጥፊ ቡድን በሁሉም የተባበረ ትግል ከሥልጣን መወገዱ የሁሉም ቀዳሚ ትኩረት መሆን ይኖርበታል፡፡ አገራችንና ወገኖቻችን እፎይታና ግልግል የሚያገኙት ብሎም ዘለቄታዊ መፍትኄ ማስገኘት የሚቻለው በአንድ የብሔረሰብ ድርጅት ወይም በተወሰኑ ድርጅቶች የተናጠል ትግል እንደማይሆን የታመነ ነው፡፡ ነብር ዥጉርጉር ቆዳውን መለወጥ እንደማይችል ሁሉ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥትም እራሱን መቀየርና ከኋላ-ቀር አምባ-ገነን አስተሳሰብ መላቀቅ እንደማይችል በተግባር ያረጋገጠ በመሆኑ፥ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ወገኖች ሁሉ በመተባበር ጭምድድ አድርጎ ከያዘው የፖለቲካ ሥልጣን መወገድ ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም ንትርክንና ክፍፍልን ትቶ አገሪቱ ያላትን አቅም ሁሉ ነባርና መሠረታዊ ችግሮች በመፍታት ላይ ለማዋል ይኸን መንግሥት መለወጥና ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ አስተዳደር መትከል ያስፈልጋል፡፡

የፖለቲካ ድርጅቶች ዴሞክራሲን በመገንባት፥ ሕዝብን ለንቁ የፖለቲካ ተሳትፎ በማብቃት እንዲሁም የሕግ የበላይነት እንዲከበር በማድረግ ረገድ የሚያበረክቱት አስተዋጽዖና የሚጫወቱት ሚና አጠያያቂ አይደለም፡፡ ያለ ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅቶች መኖርና ንቁ ተሳትፎ ሕዝቡ ጊዚያዊም ሆኑ ዘለቄታዊነት ያላቸው ጉዳዮች ላይ ያለውን ጥቅም ለማስከበር፥ ፍላጎቱን፥ ብሶቱንና ቅሬታውን በሥርዓት፥ ቀጣይነት ባለውና ሊደመጥ በሚችል መልክ ለመግለጽ፥ የሚያገኘውንም ድል ወይም ውጤት በአስተማማኝ ሁኔታ ለማስጠበቅና ለማስከበር አይችልም፡፡ እንዲሁም በገዥዎች ፍላጎት ሳይሆን ሕዝቡ በተደራጀ

ትግሉ በሚያፀድቀውና በሚቀበለው ሕገ-መንግሥት መሠረት በየጊዜው በሚደረጉ ምርጫዎች መሪዎችንም ሆነ መንግሥታዊ አስተዳደሮችን በፈረቃ ለመቀየር አይችልም:: አልፎም በአንድ ወቅት አገሪቱን እንዲመራ ኃላፊነት የተሰጠው አስተዳደር ከተሰጠው የሥልጣን ድንበር እንዳይዘል ተቀናቃኝ የፖለቲካ ድርጅቶች ሊጫወቱ የሚችሉት ሚና የሚናቅ አይደለም:: እነዚህ እሴቶች በቅጡ ሊጠበቁና ሊከበሩ የሚችሉት ግን የድርጅቶች ቁጥር ስለበዛ ሳይሆን ጠንካራና ሰፊ ማኅበራዊ መሠረትና ድጋፍ ያካበቱ ድርጅቶች የአገሪቱን የፖለቲካ መስክ ሲቆጣጠሩት ብቻ ነው:: የፖለቲካ ድርጅቶች መብዛት የዴሞክራሲ ማበብ ምልክት ቢሆን ኖሮ አገራችን በአሁኑ ጊዜ ከማንም ያላነሰች ዴሞክራሲያዊት አገር በሆነች ነበር:: እውነቱ ግን የድርጅቶች መብዛት በዋና ዋና አገራዊና ሕዝባዊ ጉዳዮች ላይ ያሉ ልዩነቶችን በማዋዋጥና በማጣጣም ተከባብሮ በጋራ መሥራት አለመቻልና የግድ አንድ ከሚያደርጉ ነጥቦች ይልቅ በትንሹም በትልቁም ልዩነት ላይ የበለጠ ትኩረት የማድረግና ያለመቻቻል ነፀብራቅ ነው:: ዴሞክራሲ በውል ሥር በሰደደባቸው አገሮች ግን ብሔራዊነትና ስፋት ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ቁጥር ከሁለትና ከሦስት አይበልጥም:: ምንም እንኳ በእነዚህ አገሮች አልፎ አልፎ ትኩረታቸው ጠባብ የሆኑ ድርጅቶች ቢኖሩም፥ ከታላላቅ ድርጅቶች በመለጠፍ ወይም የፖለቲካ ውሻል ከመሆን በቀር እራሳቸውን ችለው በአማራጭነት ለመቅረብ አቅሙ አይኖራቸውም::

የፖለቲካ ድርጅቶች፥ ቡድኖችና እንቅስቃሴዎች በአገራችን እንደ አሸን ፈልተዋል:: በአሁኑ ወቅት ከሰባ በላይ የፖለቲካ ድርጅቶች መኖራቸው ይታወቃል:: በፈለጉት መልክ መደራጀት መብት ቢሆንም ባለንበት የፈተና ጊዜ አሁን ከሚታየው ሕዝብን የሚያደናግርና እርስ በርስ ለመሻኮት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር፥ ወገን የሚለግሰውንና የሚያደርገውን አስተዋጽዖ የሚበትንና ውጤት አኮስማኝ የሆነ ይዞታ እንዲቆም ድርጅቶች እየተዋኃዱ የድርጅቶች ቁጥር በጣም እንዲቀንስ መደረጉ ጠቀሜታውና አስፈላጊነቱ ግልጽ ነው:: በየትኛውም የአገራችን ክፍል ያለ ችግር የሁላችንም ችግር ስለሆነ መፍትሔውንም በጋራ መሻትና የጋራ ራዕያችንም በጋራ እውን ማድረግ ይኖርብናል ብለን እናምናለን:: በመሆኑም የተለያዩ ብሔረ-ሰቦችን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ የቆሙና የተደራጁ ክፍሎች በኅብረ-ብሔራዊ መልክ ከተደራጁት ጋር መዋኃዳቸው ጠቀሜታው ጉልህ እንደሆነ እምነታችን ነው:: በተጨማሪም ውድ አገራችን ኢትዮጵያ በምትገኝበት የሁሉንም ዜጎች የተባበረ ትግል በሚጠይቅ እጅግ አሳሳቢ የሆነ የጋራ ኅልውና ጥያቄ በላያችን እያንዣበበ ባለበት ወቅት የድርጅቶች ያለቅጥ መብዛት አስፈላጊ አለመሆኑ ለመዋኃድ ሌላው ምክንያት ነው::

ስለሆነም አሁን በአገራችን የበቀሉት የፖለቲካ ድርጅቶችና ቡድኖች ያላቸው ምርጫ ሁለት ነው:: አንድም የዓላማና ግብ አንድነት ያላቸው ወይም የተቀራረበ አመለካከት ያላቸው ድርጅቶች በመዋኃድ ጠንካራ ድርጅት መፍጠርና ሕዝብን በሰፊው በማሰባሰብ አመርቂ ትግል ማድረግና ሕዝብን የመብቱ ባለቤት ማድረግ፤ አለያም የገዥውን ፓርቲ ዕድሜ የሚያራዝምና አገርና ሕዝብን ወዳልሆነ አቅጣጫ ከመሄድ የማያድን ፋይዳ ቢስ የቡድን ፖለቲካ መከተል ነው:: ይኸ ሲባል በአገሪቱ ያሉ ድርጅቶች ሁሉ አሁኑኑ ተጨፍልቀው አንድ ድርጅት ይሁኑ ማለት ሳይሆን፤ አብዛኞቹ ድርጅቶች ሊዋኃዱና በሁለትና በሦስት ጠንካራ ድርጅቶች ሊጠቃለሉ እንደሚችሉ በማመንና አሁን ያለው የኃይል አሰላለፍ የትም የማያደርስ መሆኑን ለመጠቆም ነው::

ኢዴኅ እና ኅብረሕዝብ የመጀመሪያውን ምርጫ እውን ለማድረግ ጽኑ እምነት አላቸው:: ዛሬ የሕወሓት/ኢሕአዴግን ፍጹም አምባ-ገነንነት ለመቋቋም የሚቻለው የድርጅቶችን ቁጥር በማብዛት ሳይሆን ድርጅቶችን ደረጃ በደረጃ ወደ ጠበቀ ግንኙነት፥ ኅብረት፥ ጥምረት ብሎም ውኅደትና አንድነት እንዲመጡ በማድረግ ነው::
በ፲፱፻፺፫ ዓ/ም አሥራ-አምስት የተለያዩ የፖለቲካ ፕሮግራሞች ያነገቡ ድርጅቶች የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረትን ሲፈጥሩ ከዓላማቸው አንዱ የኅብረቱ አባላት የሚዋኀዱበትን መድረክ ማመቻቸት ነበር:: በእርግጥም የኅብረቱ መፈጠር ድርጅቶች በቅርበት አብረው የመሥራት ባህል እንዲያዳብሩ፥ የተለያዩ ድርጅቶችን የፖለቲካ መርኃ-

እቅድ (ፕሮግራም) እና ራእይ እንዲመረምሩ፥ የተሻለ እንዲተዋወቁ፥ ተመሳሳይነታቸውን ወይም ልዩነታቸውን በደንብና በጥሞና እንዲያጤኑ፥ እንዲሁም የአሠራር ባህላቸውን በቅርብ እንዲገነዘቡ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርጓል፡፡ ስለሆነም ቀደም ብሎ ረዘም ላለ ጊዜ በዚሁ የውኅደት መንፈስ በቅርበት ሲወያዩና ሲመክሩ ከቆዩ በርካታ የኅብረቱ አባል ድርጅቶች መኻል ዛሬ ኢዴኅና ኅብረሕዝብ–ኢትዮጵያ ከረጅም ጊዜ አብሮ የመሥራትና በቅርብ የመተዋወቅ ሁኔታ በኋላ የላቀ የመተማመን ደረጃ ላይ በመድረሳቸው ትስስራቸውን አጠንክረው እነሆ ለመዋኀድ መወሰናቸውን ለሕዝብ ይፋ ማድረግ በቅተዋል፡፡

ውኅደት የተሻለ ጉልበት ነው፡፡ የተሻለ ጥንካሬንም ያስገኛል፡፡ በመሆኑም ሁለት ወይም ከዚያ ቁጥር በላይ የሆኑ ድርጅቶች ሲዋኃዱ የተፈጠረው ውኅደት ከያንዳንዳቸው የተናጠል ብቻ ሳይሆን እንዲያውም ከነሱ ነጠላ ድምር የበለጠ ይጠነክራል፡፡ ከውኅደቱ የመነጨ የሰው ብዛትና ጥራትም ይኖራል፡፡ ለአንድ ዓይነት ጉዳይ/ተግባር በብዙ ድርጅቶች አማካይነት በየፊናው የሚወጣው ገንዘብና ጉልበት አንድ ላይ ተሰብስቦ በውኅደቱ ብቻ ስለሚወጣ ያመረቃ ሥራ ለመሥራት ያስችላል፡፡ እንዲሁም በእውቀት፥ በችሎታና በተመክሮ የበለጠ ምርጫ ስለሚኖር ውኅደቱ የበለጠ ጥራት ያገኛል፡፡ በበለጠም ሁኔታ ውኅደት ዘላቂ የሆነ አገር አቀፍ ይዘትን ይሰጣል፡፡ ሁለት ብሔረሰብ ድርጅቶች ቢዋኃዱ በተናጠል ከሚኖራቸው የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል፡፡ ሆኖም እንደ አገራችን የብዙ ብሔረሰቦች ባለፀጋ ለሆነ አገር አገር–አቀፍ ይዘት እንዲኖራቸው አያስችልም፡፡ ስለሆነም ለሥልጣን የሚያበቃ ትግል ማድረግ ቢችሉም እንኳ አገር–አቀፍ ተቀባይነትና አመኔታ ማግኘት ይገዳቸዋል፡፡

በኢዴኅ እና በኅብረሕዝብ አመለካከት የውኅደት ጥቅሙ የገዥውን ዕድሜ ከማሳጠር ባሻገር፥ ድርጅቶች ያለመጠን ሲበራከቱ የሚጠፋውን ለጋራ ጥቅም ግንባታ ሊውል የሚችል የሰው አካላዊ፥ የአእምሮና የገንዘብ ጉልበትና አቅም ሁሉ አለአግባብ እንዳይባክን ይረዳል፡፡ ሕዝቡ በአጓጉል እንዳይደናገርና ለፖለቲካ ተሳትፎ ያለው ስሜት እንዳይቀዘቅዝ ሊያግዝ ይችላል፡፡ “ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ” የሚባለው የምሬት አነጋገር ከሕዝብ አንደበት ወጣም አልወጣም የሕዝቡን ትክክለኛ ስሜት ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም የድርጅቶች መብዛት የማይመልሰው ጥያቄ አለ፡፡ የአገራችን መሠረታዊ ችግሮችና የሕዝባችን ብሶቶች በአብዛኞቹ ድርጅቶች እይታ ተመሳሳይነት ካላቸው የተለያዩ ድርጅቶች መኖር ለምን አስፈለገ? የአገራችን መሠረታዊ ችግሮች የግዛታዊ አንድነት የመሸርሸር አደጋ፥ የሰብዓዊ መብቶች እንዲህ በናጠጠ መልኩ መረገጥና መጣስ፥ የዴሞክራሲያዊ አስተዳደር እጦትና የሕዝባችን ለበሽታ፥ ለከፋ ድህነት፥ ለማያባራ ረሃብና  የኑሮ ጉስቁልና መዳረግ ናቸው፡፡ ለእነዚህ ችግሮች ብሔራዊ ይዘት ያላቸው ድርጅቶች የሚሰጡት መልስ ከሞላ ጎደል አንድ እስከሆነ ድረስ በየፊናቸው እንዲቆሙ የሚያደርጋቸው ምክንያት ምንድን ነው? በተለይም እነዚህ ችግሮች ከቀን ወደቀን እየተባባሱ መሄዳቸውን የሚገነዘቡ ወገኖች ሁሉ የድርጅቶችን ውኅደት መደገፍና መግፋት የለባቸውም ወይ?

በእኛ እምነት በረባና ባልረባ ምክንያት ወይም በጠባብ ግላዊና ቡድናዊ ስሜት የአገራችን የፖለቲካ መድረክ ከመሰነጣጠቅ ይልቅ ሕወሓት/ኢሕአዴግን የሚከተለውን ፍጹም አምባ–ገነናዊ የአገዛዝ ሥርዓት ለመለወጥና ሕዝባችንን የመብቱ ባለቤት ለማድረግ ከሚደረገው ትግል አኳያ አገራችን ሊያጋጥማት የሚችለውን ጉልህ የመከፋፈልና የትርምስ አደጋ ለማስወገድ ጠንከርና መረር ላለ ብሔራዊ የአንድነት ትግል መዘጋጀትና መደራጀት ይኖርብናል፡፡ አዴኅንና ኅብረሕዝብን ለውኅደት የገፋፋቸው አንዱና ዋነኛ ምክንያት ይኸ ነው፡፡

ስለዚህ፤

- ከመቸውም ጊዜ በላይ በአገራችንና በወገናችን ላይ ያንዣበበው የአንድነት መናጋት፥ የአምባ–ገነን አገዛዝ ሥር የመስደድና ሕዝባችን እንደ ሰብዓዊ ፍጡር ሊከበሩለት የሚገቡ መብቶቹን እየተገፈፈና ክብሩ እየተገሰሰ የመቀጠል አደጋ

ይበልጥ እየከረረ፥ አስጊነቱ እየጨመረና እያየለ በመምጣቱ፤ የአገራችንንና የሕዝባችንን አንድነትና ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ሰፊ ሕዝባዊ መሠረት ያለው ቁርጠኛ ትግል ለማድረግ ጠቅለል ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች መፈጠር አስፈላጊ መሆኑን ፤

- የድርጅቶች መብዛት የአምባ-ገነኑን የሕወሓት/ኢሕአዴግን የአገዛዝ ሥርዓት ዕድሜ የሚያስረዝመው መሆኑን፤
- በአገር-አቀፍ ደረጃ ለዴሞክራሲ ግንባታ፥ ለሰብዓዊ መብትና ለሕግ የበላይነት መከበር ለሚደረግ ትግል የድርጅቶች መዋኃድ አስፈላጊ መሆኑን፤
- ድርጅቶች በአገራችን የበዙት የገዥው ፓርቲ ሆን ብሎ በለመደው የከፋፍለህ ግዛ መርኅ ምክንያት መሆኑን፤ እና
- የድርጅቶች ቁጥር መብዛት የሰው፥ የእውቀትና የገንዘብ አቅም አባካኝ መሆኑን፤

ተገንዝበን፤

እኛ የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት (ኢዴኅ) እና የኢትዮጵያ ሕዝብ ፌዴራል ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ (ኅብረሕዝብ-ኢትዮጵያ) በመኻላችን ውኅደት ለመፈጸም ረዘም ላለ ጊዜ ስናደርግ የነበረውን ሰፋ ያለ ውይይትና ዝግጅት በፍጹም መከባበርና የወንድማማችነት መንፈስ በማጠናቀቅ፤ የጋራችን ለሆነችው ውድ አገራችን ኢትዮጵያ አንድነትና ለተከበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ መብቶች መከበርና መጠበቅ የቆምንላቸውን ቅዱስ ዓላማዎች እግብ ለማድረስ የተናጠል ድርጅታዊ ኅልውናችንን መስዋዕት አድርገን እነሆ አንድ ድርጅት ለመሆን መወሰናችንን ስናበስር በታላቅ ደስታ ነው፡፡
በዚህ የውኅደት ሂደት በተለይም በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ውስጥ የምንገኝ በርካታ ድርጅቶች ለመዋኀድ ስንመክርና ስንሠራ መቆየታችን ይታወቃል፡፡ ሆኖም ውኅደቱን ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ የጋራ ጥረት ሲያደርጉ የቆዩ የትግል አጋር ድርጅቶች በአንዳንድ ጊዚያዊ እክሎች ምክንያት በአሁኑ ጊዜ የጠበቅነውና በጋራ የደከምንበትን ውኅደት ከእኛ ጋር ማድረግ አልቻሉም፡፡ ሆኖም የገጠሟቸውን ጊዚያዊ ችግሮች በቶሎ ፈትተው በቅርቡ እንደሚቀላቀሉንና እኛም አሁን ውኅደቱን ለመፈጸም ስንነሳ ይኸንኑ ታሳቢ አድርገን እንደሆነ ስንገልጽ በጠና እምነት ነው፡፡
በውኅደቱ ስምምነት መሠረት ድርጅታችን በቅርቡ የምሥረታ ጉባዔውን እንደሚያደርግና ድርጅታዊና የአሠራር መዋቅሩን እንደሚያጠናቅቅ እንገልጻለን፡፡ በአሁኑ ጊዜ ከማንም በላይ በአንድ በኩል ለወገኑ ክብር፥ ለአገሩ አንድነትና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን መሆን ከለየላቸው አምባ-ገነኖች እየተናነቀና ከፍተኛ መስዋዕትነት እየከፈለ፥ በሌላ በኩል እሱነቱን ሊያሳጡት የሚችሉ ባዕዳዊ ርካሽ ልማዶችን እየተቋቋመ ያለው የነገዋ ኢትዮጵያ ዕድል ወሳኝና ተረካቢ ወጣት የሚያደርገው ትግል ለፍሬ እንዲበቃ ድርጅቶች ልዩነቶቻቸውን አቻችለውና እየተዋኀዱ ከየራሳቸው ድርጅት በላይ አገርንና ሕዝብን ያስቀደመ እንቅስቃሴ በማድረግ ሊታደጉት ይገባል፡፡

ከአገር አንድነትና ከወገን ክብር የሚበልጥ የተቀደሰ ዓላማ የለምና ይኸን ቀናና ወሳኝ ፈለግ በመከተል፥ በፖለቲካ እይታችን ተመሳሳይነት ያለን ድርጅቶች ሁሉ በመዋኀድ የተጠናከረ ድርጅት ፈጥረን አገራችንንና ሕዝባችንን ከተደገሰለትና ከተደቀነበት የጥፋት ሂደት ለማዳን በቁርጠኝነትና በአንድነት እንድንነሳ በዚህ አጋጣሚ ለአገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች ሁሉ ወገናዊ ጥሪያችንን በአክብሮት እናቀርባለን፡፡

አንድነት ያብብ!
ኢትዮጵያ በተባበሩ ልጆቿ ቁርጠኛ ትግል አንድነቷ ይከበራል!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት (ኢዴኅ) እና የኢትዮጵያ ሕዝብ ፌዴራል ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ (ኅብረሕዝብ-ኢትዮጵያ)
ኅዳር ፳ ፲፱፻ ዓ/ም